**የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ (ኢዴኅአን)**
**Ethiopian Democratic Hibrehizb Unity Movement (EDHUM)**
P.O.Box 73796* Washington, D.C. 20056-3796
E-mail: edhum@aol.com

## ግንቦት፣ የሕዝብ ድል ብሥራት!
## የኢሕአዴግ ምርጫ ዛሬም ማላገጫ!

*የኢትዮጵያ ሕዝብ ውድ አገራችን የሕግ የበላይነት የሰፈነባትና አንድነቷ የተከበረ፣ ከቀጣይ የአምባ-ገነኖች ሥርዓት አዙሪት ተላቆ የሁሉም ዜጎቿ እኩልነት፣ ሰብአዊና ፖለቲካዊ መብቶች የተረጋገጡባት፣ እሱም የተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና የዘላቂ ሰላም ባለቤት እንዲሆን በደምና በጥሪቱ ይኽ ቀረው የማይባል መስዋዕትነት ከፍሏል፣ እየከፈለም ይገኛል። ይሁን እንጅ የናፈቀው፣ የታገለለት፣ መስዋዕት የሆነበትና አይከፍሉ ፍዳ የከፈለበትና እየከፈለበት ላለው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና ለተጠማው አስተማማኝ ሰላም ባለቤት ለመሆን አልታደለም። ይልቁንም ከአንድ ቀውስ ወደ ሌላ ቀውስ በመሸጋገር ለአሳፋሪ ቀጣይ ረሃብና ችግር፣ ለልዩ ልዩ ተውሳኮችና ተላላፊ በሽታዎች፣ ለኋላ-ቀርነት፣ ለዘግናኝ መፈናቀልና ስደት፣ ለኅብረተሰብ ባህልና ትስስር መሸርሸር ተዳርጎ የመከራ ጽዋ እንዲጎነጭ እየተደረገ በባዶ አንጀቱ ደፋ ቀና በማለት ላይ ይገኛል።*

*ለሕዝብና ለአገር ጥቅም ሳይሆን ለልመና እንዲያመቸው ብቻ በማሰብ በዴሞክራሲ ስም ሲምልና ሲገዘት የኖረው ገዥው ፓርቲ በተለያዩ ጊዚያት እንደገለጠው፣ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ መሠረት ተጥሎ ስለአበቃለት ወደ መልካም አስተዳደር መሸጋገሩንና ይኽንን ለማሳካት እንደሚንቀሳቀስ ሲያበስር እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። ታሪካዊው የግንቦት ዘጠና ሰባት ምርጫን ተከትሎ በተፈጠረው ቀውጢ ሁኔታና ቀውስ፣ ቀጥሎም በሁለተኛ ሽህ መግባደጃና በሦስተኛው ሽህ መግቢያ (ሚለንየም) ሰሞን ይኸው የመልካም አስተዳደር ሂደት በአስተማማኝ ሁኔታ መጀመሩ ተደጋግሞ ሲነገረን ነበር። ያ ለአገራዊ እርቀ-ሰላም መውረድና መግባባት ዕድል ይሰጥ ይሆናል የተባለው፣ ብዙ የተሰበከለትና ባዶ ተስፋ የተሰጠበት ታላቅ አጋጣሚም እነሆ በባዶ ቀረርቶ ተሸኘ። ገዥው ፓርቲም ለሕዝብ አስተያየት ጀሮውን ሰጥቶና የልብ ትርታውን አዳምጦ ለአገርና ለሕዝብ ጥቅም ሲባል ከተቃዋሚው ወገን ጋር ተቻችሎ ዘላቂ ሰላምንና መረጋጋትን ሊያመጣ፣ አንድነትን ሊያጠናክር ወደሚችል አቅጣጫ ያመራ ይሆናል ብለው የጠበቁ ብዙዎች እንደነበሩ ይታወቃል። ሆኖም የተጣለው ተስፋ እንደ ጠዋት ጤዛ ረግፎ እንደ ጉም ከመቅጽበት በኖ ጠፍቶ ሕዝባችን በኢሕአዴግ የተለመደ እኔ ባልኩት ሂዱ በሚል ኃላፊነት በጎደለውና ተጠያቂነት በሌለው ግትርና የለየለት የአምባ-ገነን አፈና ውስጥ እንዲገኝና አገራችን እየከፋ በሚሄድ አጠቃላይ ቀውስ ውስጥ እንድትወድቅ እየተደረገ ይገኛል።*

*ሕዝባችን ለዘመናት የተጠናወተውን ከአንድ አምባ-ገነን ወደ ሌላ አምባ-ገነን የአገዛዝ ሥርዓት ዝውውርን አሽቀንጥሮ ለመጣልና በምትኩ በነፃ ፈቃዱ በሚሰጠው ድምፅ የሚያቋቁመው ሥርዓትና የሚሰይመው መሪ ባለቤት ለመሆን ከሦስት ዓመታት በፊት በተደረገው ምርጫ ያደረገው ከፍተኛ ተሳትፎና ሰላማዊ ተጋድሎ፣ ያሳየው ብስለትና ቆራጥነት፣ ያስመዘገባቸው ድሎች በአገራችን ታሪክ ምን ጊዜም ሲታወስ የሚኖር እጅግ አኩሪ የፖለቲካ ግኝት ነበር። ያ ዓለምን ያስደነቀ አኩሪ የሕዝብ እንቅስቃሴ የኢትዮጵያ ሕዝብ በረጅም ጊዜ ታሪኩ በምርጫ ካርድ አማካይነት እውነተኛ ፍላጎቱን ያስተጋባበትና ለለውጥ ያለውን ዝግጁነት ያስመሰከረበት፣ አመፅን ኮንኖ፣ ሽብርን አውግዞና ሰላማዊ ትግልን ስልቱ አድርጎ በመንቀሳቀስ በጠንካራ መሠረት ላይ የተገነባ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለቤት ለመሆን እንደሚቻል ያረጋገጠበት፣ መሠረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ የታየበት፣ ፍላጎቱና ውሳኔውን በማያሻማ ሁኔታ የገለጸበት ታሪካዊ ክንዋኔ ነበር። ያን የመሰለ ሕዝባችንን እውነተኛ የሥልጣኑ ባለቤት ማድረግ የሚያስችልና ሁሉም ተጠቃሚና አትራፊ ለሚሆንበት የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ መሠረት የሚጥል የምልዓተ-ሕዝቡ ሰላማዊ ተጋድሎ ለፍሬ እንዳይበቃ በገዥው ፓርቲ ቁንጮዎች ሴራ በአጭር እንዲቀጭ መደረጉ በቁጭት የሚታወስ ጉዳይ ነው። የሕዝቡ ድምፅ ቢከበር ተጠቃሚው በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፈው ክፍል ብቻ ሳይሆን በገዥው ፓርቲ ወገን ያለውና በአጠቃላይም የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም ቀጣይ ትውልዶች ሁሉ ይሆኑ እንደነበር ገዥዎች ሊታያቸው አልቻለም። ተስፋ የተጣለበትና በጉጉት የተጠበቀው የሕዝብ ድል ተቀልብሶ፣ መልካም*

ጅማሮው ፈር ስቶ አገሪቱን እየከፋ ወደሚሄድ አጠቃላይ የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚና ማኅበረሰባዊ ቀውሶች እንድታመራ እየተገፋች ትገኛለች።

ታሪክና የጊዜው አጋጣሚ በፈጠረው አመች ሁኔታና ዕድል ባለመጠቀም ታሪክ ይቅር የማይለው ብሔራዊ ስህተት በመፈጸም ለሰፈነው የፖለቲካ ቀውስ ገዥው ፓርቲ ታላቁን ድርሻ አበርክቷል። እነሆ የግንቦቱ ምርጫ ቀውስ ያስከተለው የፖለቲካ አለመረጋጋትና ችግር ዛሬም ከሦስት ዓመታት በኋላ የዞረ ድምሩ ተከማችቶ ሕዝባችን ለሰሞኑ ትርጉም-የለሽና ፍሬ-አልባ ምርጫ ተዳርጓል።

የክፍለ-ከተማ፣ የወረዳ፣ የአካባቢና የማሟያ ምርጫ በሚል የተከናወነው ትርዒት ድኅረ-ግንቦት ዘጠና ሰባት የተከሰተውን ቀውስ ለማርገብና ካለፈው ስህተት ተምሮና አርሞ ወደተሻለ ሁኔታ ለመሸጋገር ሳይሆን፣ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ የመድብለ-ፓርቲ ሥርዓት እንዳይኖር ጨርሶ ለማጥፋትና ተቃዋሚን እንደ አቻ ተወዳዳሪና ተፎካካሪ ሳይሆን እንደ ዋነኛ ጠላት በመቁጠር አንበርክኮና አጥፍቶ የአንድ ፓርቲ የበላይነት ሙሉ በሙሉ የሚረጋገጥበትና ያለ ምንም ተጠያቂነት በመንግሥትና በገዥው ፓርቲ መካከል ልዩነት ሳይኖር አንዱ ለሁለቱም፣ ሁለቱም ለአንዱ በመሆን ሲያሻ አንድ አካል፣ አንድ አምሳል፣ ሌላ ጊዜ በተለይ ለውጭው ዓለም ሲያስፈልግ የተለያዩ አካሎች አስመስሎ የሚቀርብበት፣ ኢሕአዴግ ብቻውን ተወዳድሮ ብቻውን አቸንፎ በፈላጭ ቆራጭነቱ ለመቀጠል የተጠቀመበት ሌላ ሕጋዊ ሽፋን ከመሆን አያልፍም። ይኽ ደግሞ እንዲሁ የተከሰተ ሳይሆን ከምርጫ ዘጠና ሰባት ምርጫ ማግስት ጀምሮ በደንብ የተሰላ፣ ደፋ ቀና ሲልበትና ሲዘጋጅበት የቆየ ጉዳይ ነው። በዚህ ረገድ ኢሕአዴግ ከተቃዋሚው የበለጠ ከምርጫ ዘጠና-ሰባት ከፍተኛና የማይረሳ ትምህርት ቀስሟል ማለት ይቻላል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ኢሕአዴግ በብቸኝነት በሚያዘጋጀው ምርጫ ሂደትም ሆነ ውጤት እንዲሁም በምርጫ ቦርዱ ምንም ብዥታና አመኔታ እንደሌለው የታወቀ ነው። ኢሕአዴግ ሌሎች ተወዳዳሪ ድርጅቶችን በልዩ ልዩ መልክ አስፈራርቶና አግልሎ፣ አባሎቻቸውን አዋክቦ፣ እንደ መንግሥት የፖለቲካ ሥርዓቱን ጡንቻና መዋቅሩን፣ እንደ ፓርቲ ደግሞ ልምዱንና ካድሬዎቹን ተጠቅሞ እንደተለመደው ካለ ሁነኛ ተቀናቃኝ ሙሉ በሙሉ "አቸንፎ" ይዞታውን እራሱ ለራሱ አረጋግጦ የሚያልፍበት እንደሆነ ግልጽ ነው። ስለሆነም የዚህ ምርጫ ትርዒትም ውጤቱ ቀደም ሲል የታወቀና የተረጋገጠ ነበር። የዴሞክራሲ ሥርዓት ሕዝብ ነፃና ፍትኀዊ በሆነ ምርጫ መሪዎቹን የሚመርጥበትና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የሚለውጥበት፣ በፖለቲካ ሥርዓቱ ሂደትና እንቅስቃሴ በነፃነት የሚሳተፍበት፣ መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቱ የሚጠበቅበት፣ የሕግ የበላይነት የሚረጋገጥበት፣ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን መሠረት ያደረገ የሕዝብ ሥርዓት ነው። እንደሚታወቀው ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ሥልጣን ከሕዝብ መንጭቶ በሕዝብ ነፃ ፍላጎት የተመረጡት መሪዎች ኃላፊነትን ከሕዝብ በአደራነት የሚረከቡበትና የሥልጣን ዘመናቸው ሲያበቃም ለተተኪው ተመራጭ አስረክበው እንደማንኛውም ዜጋ በሰላምና በነፃነት የመኖር መብታቸው የሚከበርበትና የሚረጋገጥበት ሂደት ነው። ይኽ ሁኔታ በአገራችን እውን ሆኖ የመንግሥት ሥልጣን በአመፅና በኃይል የመቀማማቱ ዑደት እንዲያከትም የሚያስችሉ በተደጋጋሚ የተከሰቱ መልካም ታሪካዊ አጋጣሚዎች መጥተው እንደዋዛ እንዲያልፉ በማድረግ የዛሬዎቹ ገዥዎችም አሥራ-ሰባት ዓመታት በሥልጣን ላይ ከመቆየት በኋላም እንኳ በተለመደው የጥሬ ጉልበት ጎዳና መቀጠላቸው የሚያሳዝን ነው። በሕዝብ ይሁንታ የተመረጡ የሕዝብ ተወካዮችም የተመረጡበት አካል ለየግል የሥራ ዋስትና ማረጋገጫና የመታያ ቦታ ሳይሆን፣ በነፃነትና ካለአንዳች ተጽዕኖ አሳባቸውን የሚያንሸራሽሩበት፣ የሕዝብን ችግርና የአገርን ጉዳዮች ኃላፊነትን በተላበሰ መንፈስ ውይይትና ክርክሮች የሚደረጉበትና ሕጎች የሚደነገጉበት፣ አስተዳደሩ ከተሰጠው ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነት ውጭ እንዳይሄድ ቁጥጥር የሚደረግበት፣ ኤኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ እሴቶች መሠረታቸው ሳይናጋ የሚዳብሩበት፣ እያደጉና እያበቡ የሚሄዱበት ሁኔታ የሚመቻችበት፣ የሕዝብ ሥልጣን በውክልና የሚታይበት፣ ወዘተ... ከፍተኛ ኃላፊነት ማዕከል እንጂ ከሕዝብ ጋር እልህና ትንንቅ የሚገባበት፣ ተቃዋሚ እንደ ጠላት የሚታይበትና በሰጠው አስተያየት የሚወገዝበት፣ ወደ ጠርዝ የሚገፋበትና አገር-ነክ የሆኑ ጉዳዮች እንዳልባሌ የሚታዩበት የቀልድ መድረክ አይደለም።

ገዥው ፓርቲ ኢሕአዴግ አሁን የሚከተለው አሠራር ካልተገታ ለዴሞክራሲ ሂደት ግንባታ ፀር ከመሆኑም ሌላ በየጊዜው እየከፋና ይበልጥ እየተወሳሰበ የመጣውን የአገራችን ሁኔታ፣ "ከድጡ ወደ ማጡ" እንዲሉ፣ እንዲባባስና ሕዝባችንን ለበለጠ አደጋ እንዲጋለጥ ያደርል የሚል ከፍተኛ ስጋት አለን። በዚህ የጥፋት ጉዞ መቀጠሉ በታሪክ ተጠያቂ ከመሆን ሌላ ለገዥዎቹም እንደማይጠቅም ከቶውንም ሊረዱት የቻሉ አይመስልም።

በአንዳንድ አገሮች እንደሚታየውና እንደሚሰበከው "ለአንድ ታዳጊ አገር ብዙ ፓርቲዎች አያስፈልጉም፣ አንድ ጠንካራ ፓርቲ በቂ ነው" በሚለው እምነት የኢሕአዴግ ገዥዎችም አገራችንን ወደዚያው እየወሰዷት እንደሆነ ብዙ ምልክቶች ይታያሉ። ይኽ አመለካከት ሕዝብ የሥልጣን

ምንጭና የአገራዊ ሉዓላዊነት ባለቤት መሆኑን ቁጥር ውስጥ ያላስገባ፣ ሕዝብ ተገልጋይ ሳይሆን ገዥው እንደፈለገው ሊገለገልበት የሚችል አድርጎ የሚቆጥር፣ አገሪቱን፣ ሕዝቧንና ጥሪቷን ሁሉ ለአንድ ፓርቲ ቁንጮዎች የግል ሃብትነትና ሙሉ ቁጥጥር አሳልፎ የሚዳርግ አደገኛ አካሄድ ነው። ከወዲሁ ሕወሓት/ኢሕአዴግ ለአለፉት አሥራ-ሰባት ዓመታት የአገሪቱ ጠቅላላ መሬትና፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የአብዛኛዎቹ የንግድና የኢንዱስትሪ ተቋማት ባለቤት፣ በአጠቃላይ የአገሪቱ ሀብት አዛዥ ናዛዥ መሆኑና ቢያንስ በአፍሪቃ ውስጥ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ሃብታም የፖለቲካ ድርጅት መሆኑ ግልጽ እንደሆነ እየታወቀ፣ በምርጫ ስም ሌሎች ድርጅቶች እንዲከስሙ በማድረግ ቀስ በቀስ በአገሪቱ የፖለቲካ ሕይዎት ውስጥ ብቸኛው ተዋናይ የመሆን አቅጣጫን ተያይዞታል።

የሕዝብን አመኔታ ካጣው ምርጫ ባሻገር አሁን ያለንበትን ሁኔታ ስንመረምር በአንድ በኩል ኢሕአዴግ በለመደውና በተጠናወተው ሕዝብን የናቀ አካሄዱ ከሕዝብ ይበልጥ እየተነጠለ፣ ይበልጥ በእብሪት የተወጠረ አምባ-ገነን እየሆነ እንደሚሄድ ስናይ፣ በሌላ በኩልና በአኳያው በአገራችን ያለው ሁለንተናዊ ቀውስ ይበልጥ እየከፋና ሕዝባችን እጅግ ለመረረ ችግርና አደጋዎች እየተጋለጠ እንደሚሄድ እንገነዘባለን። በዚህ ረገድ በተቃዋሚው ጎራ የሚታየው ትርምስና አቅጣጫ የሳተ ይዞታ ለችግሩ አስተዋጽዖ እንዳለው እንረዳለን። ጠንካራ፣ የተባበረና የጠራ የትግል ስልትና ስትራቴጂ የሚከተል ተቃዋሚ እጦት ለአምባ-ገነን ሥርዓት ማቆጥቆጥ፣ ማበብና መስፈን ቀጥታ አስተዋጽዖ እንዳለው ግልጽ ነው። ጉዳዩን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠበቅበትን አድርጓል፣ አሁንም አላቋረጠም፣ ለማድረግም ቁርጠኝነት አለው። ለመልካም ሥርዓት ግንባታ ያደረገውን ከባድ ተጋድሎና የከፈለውን ክቡር መስዋዕትነት የሚመጥን ድርጅታዊ ብቃትና ቁርጠኝነት ያለው፣ አስጀምሮ የሚያስጨርስ መሪ ድርጅት እጦት ግን አሁንም በጣሙን ገዶታል። ይኸንን መራር ሃቅ መቀበል የግድ ይሆናል። ሁሉም ከተናጠል ጉዞው ቆም ብሎ ሁኔታውን ከልብ ማጤንና መፍትኄውን በጋራ ማፈላለግ ያስፈልጋል ብለን እናምናለን።

የሕዝብን የማወቅና አሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ገድቦ፣ ቅድመ-ግንቦት በነበረው መጠነኛ ክፍተት ባለሙያዎች ባደረጉት መሰል የሌለው ተጋድሎና መስዋዕትነት እያቆጠቆጠ የነበረውን የነፃው ሕትመትና ስርጭትን (ፕረስን) ገዥው ፓርቲ አፍኖና የመገናኛ ብዙኃንን ጭምድድ አድርጎ በብቸኛነትና በሙሉ ቁጥጥሩ ሥር ባደረገበት፣ መሠረታዊ የሚባሉ ሰብዓዊ መብቶች ሳይቀሩ አዘቦታዊ በሆነ መንገድ በሚጣሱበት፣ የፍትኅ ሥርዓቱ ዓይን ባወጣ መልኩ የገዥው ፓርቲ ፈቃድና ፍላጎት ማስፈጸሚያና መገልገያ መሣሪያ በሆነበት፣ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ነፃ (ገለልተኛ) ተቋማት እንዲወድሙ በተደረገበትና በተለጣፊዎች በተተኩበት፣ ሙስና ጣራ በነካበትና የሕዝብን ንብረት ከብሔራዊ ባንክና ከመንግሥት ግምጃ ቤቶች መቆንጠር ሳይሆን በማፍያዊ አሠራር ዘይቤ በገፍ በሚዘረፍበት፣ የኑሮ ውድነት ጣራ ነክቶ ሕዝባችን ለናጠጠ ችግር በተዳረገበት፣ ከዘጠኝ ሚሊዮን የማያንስ ሕዝባችን እንደገና ለዘግናኝ ረሃብ እየተዳረገ ባለበት፣ ሥራ-አጥነትና መፈናቀል ከዕለት ዕለት በአስደንጋጭ ፍጥነት ሽቅብ እየወጡ በሚገኙበት፣ ዜጎች ተስፋቸውን አሟጠው በምሬት አገራቸውን ጥለው ለመውጣት በሚያደርጉት ጥረት ታይቶ የማይታወቅ ሰቆቃ በሚቀበሉበት፣ የነገዋ አገር ተረካቢና ተስፋ የሚባሉት ታዳጊ ልጆችና ለጋ ወጣቶች ሳይቀሩ ለጎዳና ተዳዳሪነትና ክቡር ገላቸውን እንዲሸጡ የተገደዱበት አሳፋሪና አስቆጭ ይዞታ ላይ በወደቁበት፣ በአንድ አገር ጥላ ሥር ተቻችሎና ተከባብሮ የኖረ ሕዝብ (በቅርቡ በአንዳንድ ቦታዎች እንደተከሰተው) በጎሣና በሐይማኖት ምክንያት ልዩነትና ቅራኔ እንዲባባስ እየተደረገ ሕዝብን ወደ ትርምስ ለሚወስድና አገራዊ አንድነት የበለጠ እንዲሸረሸር የሚያደርጉ ሁኔታዎች እየተመቻቹ ባሉበት፣ አገራችን ከአካባቢያዊ አልፎ ዓለም-አቀፍ ይዘትና እጅግ አደገኛ ጦስ ወዳለው ጦርነት ውስጥ እንድትዘፈቅ በተደረገበት፣ ወዘተ... ወዘተ... ሁኔታ አላጋጨ ኢሕአዴግ የአገሪቷ ኤኮኖሚ በሁለት አሓዝ እንዳደገ፣ ለተከታታይ ዓመታትም እድገቱ በተመሳሳይ ቁጥር እንደሚቀጥል፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እያበበ እንደሚገኝ፣ ወዘተ... በመግለጽ ላይ ይገኛል። አልተገናኝቶም ይሏል ይኸ ነው!

ኢሕአዴግ የሚፎክርበት የኤኮኖሚ እድገት በኢትዮጵያውያን ላይ ካልታዬ ምን በላው? አንዳንዴም የሚሰጠው ምክንያት በውነቱ የሚገርም ነው። ኢሕአዴግ በአገራችን ያሉትን ዙሪያ ጥምጥም ችግሮች በቅርቡ በዓለም ከተከሰተው የነዳጅ ዋጋ ንረት ጋር ለማያያዝ ሲሞክር እየተስተዋለ ነው። ለዚሁም በዓለም ላይ በተለይም በታዳጊ አገሮች የተከሰተውን የምግብ እጥረት በተመለከተ በቅርቡ ቢቢሲ ያጠናቀረውን ዘገባ በመቆራረጥ በሕዝባችን ላይ እየደረሰ ያለው ችግር የዓለም-አቅፍ ሕዝብም እየደረሰበት ያለ መሆኑን አበክሮ ለማሳመን ሞክሯል። ትርጉሙም ለሕዝባችን ችግር ኢሕአዴግና በሱ የሚመራው መንግሥት ተጠያቂ አይደለም፣ ችግራችሁን ቻሉት፣ አታማርሩ፣ አርፋችሁ ተቀመጡ የሚል መሆኑ ነው።

በገሃድ የሚታዩና በአብዛኛው ኢሕአዴግ በሚከተላቸው አገርንና ሕዝብን ባላስቀደሙ ብቻ ሳይሆን ጨርሶ ባላቋጠሩና አልፎም በሚጻረሩ መርኃ-እቅዶች (ፖሊሲዎች) ምክንያት ለተፈጠሩ ችግሮች የጋራ መፍትኄ እንደመሻትና ሁኔታውን ተገንዝቦ ሕዝብን አስተባብሮ መልስ እንደ መፈለግ፣ ገዥው ፓርቲ በተለመደ እልህና እብሪት ጉዳዩን አቃልሎ ማየትንና እንደ ጲላጦስ ጨርሶ ከደሙ ንጹኅ ነኝ ብሎ መቀመጥን የመረጠ ይመስላል፡፡

ከየትም ሆነው ቢመለከቱት፣ በማንኛውም መስፈሪያ ቢለኩት ፈርጀ-ብዙ፣ መጠነ ሰፊና ይበልጥ እየተወሳሰበና እየከፋ የሚሄደውን የአገራችን ዙሪያ ጥምጥም አሳሳቢ ችግር ለመፍታት የሚቻለው ሕዝቡን የሥልጣኑ ባለቤትና የራሱ ዕድል ወሳኝ እንዲሆን ዴሞክራሲን በትክክል በሥራ ላይ በማዋል እያንዳንዱ ዜጋ በአገሩና በራሱ ጉዳይ ሙሉ ተሳታፊ የሚሆንበት ሁኔታ ሲመቻች ብቻ ነው፡፡ እነሆ ዛሬ በኢትዮጵያችን ጭላንጭል ፈንጥቆ የነበረው የዴሞክራሲ ሥርዓት ለምን እንደተቀለበሰና እንደተደናቀፈ ከሊቅ እስከ ደቂቅ፣ ከከተማ እስከ ገጠር ለማንም የተሰወረ አይደለም፡፡ ማን ለእውነተኛ ዴሞክራሲ፣ ለሕግ የበላይነት፣ ለፍትኅ፣ ለእኩልነት፣ ለብሔራዊ ጥቅምና ለአገራዊ አንድነት እንደቆመና እንደሚታገል፣ ማን ለውጭ እረዳቶች መሸንገያ ያኽል ብቻ የዴሞክራሲን የማስመሰያ ጭምብል አጥልቆ ውጤቱ አስቀድሞ በተወሰነ “ምርጫ” አምባ-ገነን ሥርዓትን ለማስፈን እንደተንቀሳቀሰ ባለፉት አሥራ-ሰባት የኢሕአዴግ አገዛዝ ዓመታት በገሃድ ተረጋግጧል፡፡

የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ የኢትዮጵያ ሕዝብ በግንቦት ዘጠና-ሰባት ያደረገውን ታሪካዊ እንቅስቃሴ፣ የከፈለውን ይኽ ቀረው የማይባል መስዋዕትነትና ያስመዘገባቸውን ድሎች ሲዘክር፣ ክቡር ሕይዎታቸውን ላጡ፣ በእስር ለተንገላቱና ለሚንገላቱ፣ ከሥራቸው፣ ከኑሮአቸው፣ ከቤተሰባቸው አልፎም ከአገራቸው ለተፈናቀሉ፣ መዳረሻቸው ለጠፉ ወገኖቻችን ሁሉ ያለንን ልባዊ አድናቆትና ከፍተኛ አክብሮት በመግለጽ ነው፡፡ እነኝህ ሰማዕታት አገራችንን ለሁሉም የሚበጅ የተሻለ ሥርዓት ባለቤት ለማድረግ በተደረገ ትግል በከፈሉት መስዋዕትነት አኩሪ ታሪካቸውን ጽፈዋልና በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ምን ጊዜም ኅያው ሆነው ይኖራሉ፡፡
በዚህ ሕዝብን የሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን ለማስቻል በሚደረግ ቀጣይ የአንድነትና የጋራ ትግል በውጭም በውስጥም ያለው ኢትዮጵያዊ በተለይም ወጣቱ ክፍል ያደረገውና የሚያደርገው ያላሰለሰ እንቅስቃሴ መሰል የሌለውና ይበጅ የሚያሰኝ እንደመሆኑ፣ በአንዳንድ ክስተቶች ተስፋ ሳይቆርጥ አሁንም ጥረቱን እንዲገፋበት ጥሪያችንን በአክብሮት እናቀርባለን፡፡

ወቅቱ የመኳነኛና የመወነጃጀያ ሳይሆን አገርንና ሕዝብን ከአንዣበበ የትርምስ አደጋና ቀውስ አድኖ ለሁሉም ለሚበጅ ሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሁኔታን ማመቻቸት ስለሆነ፣ በቅድሚያ ከራስ ታርቆና ልዩነትን አቻችሎ፣ ከግል፣ ከቡድንና ከድርጅት በላይ ለሆኑት ለአገርና ለሕዝብ ቅድሚያ በመስጠት ለጋራ ችግሮቻችን የጋራ መፍትኄ ለመፈለግ ቁርጠኝነቱና ውሳኔው ሊኖረን ይገባል ብለን እናምናለን፡፡ ዛሬም ሆነ ምን ጊዜም ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ፣ ለፍትኅ፣ ለሕግ የበላይነት፣ ለእኩልነት፣ ለሰብዓዊ መብት መከበርና ለአንድነት የሚደረገው ትግልና ሂደት የቱንም ያኽል አስቸጋሪ ቢሆንና ፈተና ቢበዛበትም የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ የአንድነት ንቅናቄ (ኢዴኅአን) በሁሉም ዘርፍ የተሻለች አገርን ለቀጣይ ትውልዶች ለማስረከብ ኢትዮጵያን ማዕከል አድርጎና የሕዝብን አጀንዳ አንግቦ በትግሉ መቀጠሉን ለአፍታም ቢሆን ቸል የማይለው ጉዳይ እንደሆነ ማረጋገጥ እንወዳለን፡፡
የግንቦት ድሎችንና ለነሱም የተከፈለውን መስዋዕትነት በምንዘክርበት በዚህ ወቅት፣ አገራችንና ሕዝባችን ያሉበትን አደገኛ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች፣ የሲቪክና የሙያ ማኅበራትና ስብስቦች ሁሉ ካለፈው ተምረው፣ ልዩነቶቻቸውን አቻችለውና አዋውጠው በአስቸኳይ እንዲሰባሰቡና በጋራ እንዲታገሉ ወገናዊ ጥሪያችንን በድጋሜ እናቀርባለን፡፡

ሰማዕታትን በጋራ እንዘክር!
አንድነት ኃይል ነው!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኅብረሕዝብ አንድነት ንቅናቄ (ኢዴኅአን)
ሚያዝያ ፲ ቀን ፪ ሺህ ዓ/ም